# Learning by Ear 2013

**«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 9: ትክክለኛው ውሳኔ ይሆን?

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Daniel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: AT THE MSOTOS’**

- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 2: ምህረት AT ዶ/ር ዘሪሁን’S**

- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **SAD MOTHER (F, 40)**
- **ዶ/ር ዘሪሁን (M, 45)**

**SCENE 3: ቅዱስ NAPS, DREAMS**

- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **ቅዱስ (M, 8)**
- **ብሩክ (M, 8)**
- **MAN (M, ADULT)**

- **MAN 2 (M, ADULT)**

**SCENE 4: IN THE STREETS**

- *ምህረት* **(F, 15)**
- **SAD MOTHER (F, 40)**

**INTRO**

**1. NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች፡፡ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" የተሰኘው ተከታታ ድራማችን ነው፡፡–«መዘዙን መቀበል» የሁለተኛው ዙር ድራማርዕስ ነው ፡፡ እስኪ እስካሁን የሆነውን መለስ ብለን እንቃኝ፡ መንትዮቹ ቅዱስ እና ብሩክ ጎረቤት ሀገር ላቦሪያ ውስጥ በግዳጅ ይሰሩ ከነበረበት የማዕድን ማውጫ አምልጠው ተመልሰዋል፡፡ ሁለቱም ልጆች አዛ በገጠማቸውመጥፎ ድርጊት ትውስታ አሁንም እየተሰቃዩ ነው ፡፡ታላቅ እህታቸው ምህረትም እንዲሁ ችግር ውስጥ ናት፡፡ እናቷ እርጉዝ መሆኗን ደርሰውበታል፡፡

**2. EPISODE 8, LINES 111 - 116:**

*ወ/ሮ ሉሊት: ንገሪኝ ብያለሁ፡፡ አሁን ሶስተኛ ቀንሽ ነው ጠዋት ላይ ሲያስመልስሽ፡፡ ምልዕክቶቹን አውቃለሁ፡፡ (…)*

***108.*** *ምህረት: ይቅርታ እማዬ ይህ እንዲከሰት ፈልጌ አልነበረም…*

**3. NARRATOR:**

የምህረት የክፍል ጓደኛ ዳንኤል ያልተወለደው የምህረት ልጅ አባት ነው፡፡ ችግሩን ለመፍታት ግልፅ ሀሳቡን አስቀምጧል፡፡ ይህም ምህረት ፅንሱን ማስወረድ አለባት የሚል ነው፡፡ የምህረት ጓደኛ ትዕግስትም በእዚሁ ሀሳብ yteስማማለች፡፡ ሆኖም ትዕግስት ይህንን የምትልበት የራሷ ምክንያት አላት፡፡

**4. EPISODE 6, LINES 9 – 11:**

*ትዕግስት: የጠየኩዎት እኮ በጣም ትንሽ ገንዘብ ነው ዶክተር ዘሪሁን! (…)*

*ዶ/ር ዘሪሁን: አዝናለሁ ትዕግስት። ውል፤ ውል ነው። የተስማማነው ፅንስ ማስወረድ የሚፈልጉ ወጣት ሴት ልጆች ስታመጪልኝ እንደምከፍልሽ ነው። ያለ ልጆች— ገንዘብ የለም።*

*ትዕግስት: እናክዎን ዶ/ር ዘሪሁን…*

**5. NARRATOR:**

ምህረት የዳንኤልን እና የትዕግስትን ምክር ትከተል ይሆን? እስቲ ዛሬ ከእናቷ ጋ ስታወራ እንስማቸው። ርዕሱ «ትክክለኛው ውሳኔ ይሆን?» ይሰኛል።

**<u>SCENE 1: AT THE MSOTOS</u>**

**6. SFX: ATMO TANDIKA SLUMS: INTERIOR, DAYTIME,**

**7.** ወ/ሮ ሉሊት: **(firm)** ምህረት! ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ የምልሽ ነገር ቢኖር ልጁን የሚጎዳ ነገር እንዳታደርጊ። የእናትነት ምክር ነው የምለግስሽ!

**8.** ምህረት: **(desperate)** እማዬ። እኔም እንደዛ ቢሆን ደስ ይለኛል። ግን ማድረግ ይኖርብኛል። ትምህርቴን መቀጠል እፈልጋለሁ። ጀርባዋ ላይ አዝላ ትምህርት ቤት የምትሄድ ልጅ አይተሻል?

**9.** ወ/ሮ ሉሊት: ምህረት ለእዚህ መፍትሄ አይጠፋም። ርዕሰ መምህርቷ በዚህ የተነሳ ታባርርሻለች ብዬ አላስብም። ላንቺ ትራራልሻለች።

**10.** ምህረት: **(cries)** ይህ በፍፁም ሊሆን አይችልም። ርዕሰ መምህርት ሰብለ እርጉዝ እንደሆንኩ ካወቁ ያባርሩኛል። **(sobs)** በዛ ላይ እናት ለመሆን አሁን ዝግጁ አይደለሁም።

**11.** ወ/ሮ ሉሊት: ግን ዳንኤል ከምትይው ልጅ ጋ ለመተኛት ዝግጁ ነበርሽ። አይደለም እንዴ?

**SILENCE**

**12.** ወ/ሮ ሉሊት: ስለሆነም መዘዙን መቀበል አለብሽ! ልጁን ትወልጃለሽ። አለቀ።

**13.** ምህረት: **(loses it)** ከኔ ምንድን ነው የምትፈልጊው? እያንዳንዱ ሰው ከኔ ምንድን ነው የሚፈልገው? ለምን ሁላችሁም ሰላም አትሰጡኝም።

**14. SFX: FOOTSTEPS - ምህረት GOING AWAY**

**15.** ወ/ሮ ሉሊት: ምህረት? ነይ ተመለሽ።

**16. SFX: DOOR IS OPENED AND CLOSED**

**17.** ወ/ሮ ሉሊት: **(Shouts after her)** የምናገረው ግልፅ መሰለኝ።

**18. MUSICAL INTERLUDE (tense building music)**

**SCENE 2: ምህረት AT ዶ/ር ዘሪሁን'S**

**19. SFX: STREET ATMO**

**20.** ትዕግስት: ምህረት! መጣሽ?! በስልክ ድምፅሽ በጣም የተጨነቀ ይመስል ነበር!

**21.** ምህረት: እህ! ትዕግስት...እየረዳሽኝ በመሆኑ እድለኛ ነኝ። ብታይ ላብድ ትንሽ ነው የቀረኝ። እናቴ ምንም ልትረዳኝ አልቻለችም።

**22.** ትዕግስት: ብቻ ዋናው ነገር አንቺ አንድ ውሳኔ ላይ መድረስሽ እና ሀሳቤን መቀበልሽ ነው። ነይ እንግባ።ዶ/ር ዘሪሁን እየጠበቀን ነው።

**23.** ምህረት: ቆይ። ውስጥ ሰው አለ።

**24. SAD MOTHER: (heard shouting from inside)** አያፍሩም እንዴ? ልጄን እኮ ነው የገደሏት። ህሊናዎ እንዴት እሺ ይልዎታል?

**25.** ዶ/ር ዘሪሁን: ስራዬን ነው ያከናወንኩት። አለቀ!

**26. SAD MOTHER:** ህፍረት ይሰማዎ! እረግሜዎታለሁ ዶክተር ዘሪሁን። እረግሜዎታለሁ።

**27. SFX: DOOR OPENS QUICKLY, FOOTSTEPS AS WOMAN LEAVES AND PASSES** ምህረት **AND** ትዕግስት

**28.** ዶ/ር ዘሪሁን: **(from inside, trying to adopt a friendly tone)** እንዴት ናቹህ ልጆች ግቡ ወደ ቢሮዬ።

**29.** ምህረት: **(whispers)** ትዕግስት ፤ በጣም ነው የፈራሁት። ሴትየዋ ያሉትን ሰምተሻል አይደል?

**30.** ትዕግስት: ምህረት፤ እረ እንደዚህ አታጋኚ።

**31. SFX: FOOTSTEPS ምህረት AND ትዕግስት**

**32. SFX: DOOR CLOSES**

**33. SFX: TRAFFIC HEARD THROUGH DOOR**

**34.** ዶ/ር ዘሪሁን: እሺ ምህረት። በመጨረሻ አንድ ውሳኔ ላይ ደረሽ።

**35.** ምህረት: እ... እኔ...

***KW BEGIN***

**36.** ትዕግስት: ማድረግ እንደምትፈልግ ነግሬዎታለሁ።

**37.** ዶ/ር ዘሪሁን: በርግጥ ይህ በህይወትሽ ያደረግሽው ትክክለኛ ውሳኔ እንደሆነ አረጋግጥልሻለሁ ምህረት።በፍፁም አትፀፀቺም።

**38.** ምህረት: እኔንጃ... እኔ...

**39.** ትዕግስት: ጓደኛዬ አስተዋይ ናት። ህይወቷን ባልተፈለገ እርግዝና ልታመሰቃቅል አትፈልግም።

***KW END***

**40.** ዶ/ር ዘሪሁን: ጥሩ እንግዲያውስ እንጀምር? የቀዶ ጥገና ጠረቤዛው ላይ ትወጪ... ቆይ እኔ እረዳሻለሁ።**(acts out lifting her)**

**41.** ምህረት: አይ ቆይ! **(shocked)** ይህንን ቢለዋ ነው የሚጠቀሙት? እላዩ ላይ ደም አለ።

**42.** ትዕግስት: ኧረ ምህረት እንደዚህ አትረብሺ። ብዙ ሴቶች ይህንን አልፈውበታል።

**43.** ዶ/ር ዘሪሁን: ምህረት የምሰራውን እንደማውቅ ላረጋግጥልሽ እወዳለሁ።

**44.** ምህረት: **(firm)** አይ ሀሳቤን ቀይሬያለሁ። ማስወጣት አልፈልግም።

**45. SFX: RUSTLING OF CLOTHES AS ምህረት GETS UP**

**46. SFX: RUNNING FOOTSTEPS**

**47. SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

**48.** ትዕግስት/ዶ/ር ዘሪሁን: ምህረት ቆይ እንጂ!

**49. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: ቅዱስ NAPS AND DREAMS</u>**

**50. SFX: TANDIKA SLUMS INSIDE, DAYTIME**

**51.** ቅዱስ: **(snores lightly)**

**52. SFX: ወ/ሮ ሉሊት WASHING THE DISHES (NO RUNNING WATER)**

**53.** ወ/ሮ ሉሊት: **(to herself)** ወይ ጉድ! ምህረት ዛሬ ጠዋት ካናገርኳት በኋላ ወዴት ሄዳ ይሆን? **(to ቅዱስ)** ቅዱስ እስኪ ማድረቂያውን ጨርቅ ስጠኝ**(silence)** ቅዱስ?

**(to herself)** እውይ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወስዶታል። ይተኛ ልተወው…

***KW BEGIN***

**54. SFX: SLUM ATMO FADE OUT, TOWN ATMO WITH TRAFFIC FADE IN**

**55. SFX: DREAM SEQUENCE - ALL VOICES WITH ECHO**

**56. ብሩክ:** ለውዝ እንሸጣለን ለውዝ የሚገዛ!

**57. ቅዱስ:** ለውዝ 50 ሳምቲም። ለውዝ በ50 ሳንቲም ብቻ!

**58. SFX: CAR STOPPING, ENGINE STILL RUNNING**

**59. SFX: KNOCK ON CAR WINDOW**

**60. SFX: CAR WINDOW ROLLS DOWN**

**61. ቅዱስ:** አባባ ለውዝ ይግዙኝ። 50 ሳንቲም ብቻ።

**62. MAN:** ሶስት እሽግ ስጠኝ

**63. SFX: PAPER NOISE AS GROUNDNUTS HANDED OVER**

**64. ብሩክ:** 1.50.

**65. SFX: CAR HORNS**

**66. MAN 2:** **(from behind)** አንተን እኮ ነው! ጥፋ ከዚህ!

**67. SFX: CAR WINDOW ROLLS UP**

**68. SFX: CAR DRIVES AWAY**

**69.** ብሩክ: ኧረ ቅዱስ ተመልከተው፤ መኪናውን አስነስቶ ሊሄድ ነው! **(shouts)** ኧረ - ገንዘባችንን ይስጡን።

**70. SFX: CARS HORNS HONK**

**71.** ቅዱስ: ተከተለው ሩጥ! ብሩክ, ሩጥ! ብሩክ!

**72. SFX: ATMO TANDIKA SLUMS FADE IN, ECHO STOPS**

***KW END***

**73.** ቅዱስ: **(continues crying sleepily)** ሩጥ, ብሩክ! ሩጥ, ብሩክ!

**74. SFX:** ወ/ሮ ሉሊት **SHAKING** ቅዱስ

**75.** ወ/ሮ ሉሊት: አንተ! ቅዱስ እስኪ ንቃ! በህልምህ ነው። ለምንድን ነው ወንድምህን ሩጥ የምትለው?

**76.** ቅዱስ: **(still sleepy)** ያንን ሰውዬ በድጋሚ በህልሜአይቼው ነው።

**77.** ወ/ሮ ሉሊት: የቱን ሰውዬ?

**78.** ቅዱስ: ለውዛችንን ስለሰረቀው።

**79.** ወ/ሮ ሉሊት: ስለእሱከዚህ ቀደም አልነገርከኝም። ምንድን ነው የሆነው?

**80.** ቅዱስ: ብሩክ እና እኔ ከማዕድን ማውጫው ጠፍተን ወደ ከተማ የሄደን ጊዜ የምንበላው አልነበረንም። ከዛ ልክ እንደኛ ጎዳና ላይ የሚኖሩ ልጆች ተመለከትን። ለውዝ ይሸጡ ነበር። ከዛ ስራ እንዲያሰሩን ጠየቅናቸው።

**81.** ወ/ሮ ሉሊት: እና አሰሩዋቹህ?

**82.** ቅዱስ: አይ ግን እነሱ ከበረከት ጋ አስተዋወቁን። በረከት ከሁሉም ትልቁ ነው። እና በምግብ ፋንታ፤ ትልቅ ሰሀን ሙሉ ለውዝ እንድንሸጥ ሰጠን። ግን ሁሉንም ገንዘብ በትክክል ካላስረከብሽ ይደበድብሻል።

**83.** ወ/ሮ ሉሊት: ምን? ወይ አምላኬ! እውነቱን ንገረኝ አንተን ወይንም ብሩክን ነክቶዋችሁ ያውቃል?

**84.** ቅዱስ: አያውቅም! ባለመኪናው ሰውዬ ሳይከፍለን ስላመለጠእኮ ነው እኛም ተከትለነው በዛው ያመለጥነው። ግን የከባድ መኪና ሹፌሩ አቶ ደንበል ወደ ቤታችን ባያደርሱን ኖሮ እና በረከት ቢያገኘን ኖሮ በእርግጠኝነት ይመታን ነበር።

**85.** ወ/ሮ ሉሊት: **(deeply moved)** አይ አምላኬ። ቅዱስ አንተና ብሩክ ይሄ ሁሉ ነገር ስለገጠማችሁ በጣም አዝናለሁ። ግን እክስታችሁ ለምለም ይህ ሁሉ ሲሆን የት ነበረች?

**86.** ቅዱስ: እዛ ማዕድን ማውጫ ያለው ሰውዬ ጋ ከወሰደችን ጊዜ አንስቶ አላየናትም።

**87.** ወ/ሮ ሉሊት: **(to herself)** ብቻ ያገኘኋት ቀን… **(to ቅዱስ)** ቅዱስ አይዞህ ምንም አይነት ስጋት አይግባህ። እዚህ ምንም አትሆን።

***KW BEGIN***

**88.** ቅዱስ: ውጪ ወጥቼ ከብሩክ ጋ መጫወት እችላለሁ? ተመልሼ ተኝቼ እነዛን ምስሎች ማየት አልፈልግም።

**89.** ወ/ሮ ሉሊት: እሺ የኔ ልጅ!

**90. SFX: FOOTSTEPS ቅዱስ**

**91. ወ/ሮ ሉሊት:** **(to herself)** ይህቺ መተተኛ ለምለም! ልጆቼን አሳድጋለሁ ብላ ወስዳ እንዲህ ማዕድን ማውጫ ውስጥ ፍዳቸውን ታብላቸው። የገዛ የወንድሞቿን ልጆች ምን እንደሆኑ እንኳን አያሳስባትም። ። እንደው ምን አይነት ቤተሰብ ውስጥ ነው የጣለኝ በፈጣሪ?

***KW END***

**92. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: IN THE STREETS</u>**

**93. SFX: STREET ATMO (SAME AS IN FRONT OF ዶ/ር ዘሪሁን’S)**

**94. SFX: ምህረት’S RUNNING FOOTSTEPS**

**95. ምህረት:** **(panting, to herself)** አልቻልኩም። በቃ ላደርገው አልቻልኩም…

**96. SFX: ምህረት BUMPS INTO ANOTHER PERSON**

**97. SX: FOOTSTEPS STOP**

**98. SAD MOTHER:** የምትሄጅበትን አያየሽ። ልትወጨ.ብኝ ነበር እኮ።!

**99. ምህረት:** **(breathless)** ይቅርታ አላየዎትም ነበር።…

**100.SAD MOTHER: (recognizes her)** አንቺን እና ጓደኛሽን እዛ ገዳይ ቤት አይቻችኋለሁ።

**101.** ምህረት: ገዳይ? የምን ገዳይ?

**102. SAD MOTHER:** እዛ ክሊኒክ ተብዬው ውስጥ። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት!

**103.** ምህረት: ዶ/ር ዘሪሁንን ማለትዎ ነው?

**104. SAD MOTHER: (disrespectful)** ሰውየው ዶክተር አይደለም።

**105.** ምህረት: **(confused)** አልገባኝም…

**106. SAD MOTHER: (taking a deep breath)** ልጄ ማርገዟን ስታውቅ 17 አመቷ ነበር! እሷስ ልጁን ልትወልድ ፈልጋ ነበር። እኔ ነኝ እንጂ እንድታስወርድ ያደረኩ…ለእዚያውም እዚያ ዶክተር ነኝ ባይጋ። እንደሚረዳት ቃል ገብቶልኝ ልጄን ዳግም እንዳላያት አደረገብኝ። **(breaks down)** የገዛ ልጄን ገደልኳት።

***KW BEGIN***

**107.** ምህረት: ውይ! እንዴት ይሰቀጥጣል። በጣም አዝናለሁ…ምን ሆና ነው?

**108. SAD MOTHER: (trying to pull herself together)** ከነካካት በኋላ በኋላ ብዙ ደም ፈሰሳት። አስቀድሜ ማወቅ ነበረብኝ። ሰዎች እዚህ ሰውዬ ጋ እንዳትወስጃት ብለው አስጠንቅቀውኝ ነበር።ግን እኔ ያስጨንቀኝ የነበረው ማህበረሰቡ የሚለው እንጂ የልጄ ህይወት አልነበረም። **(weeps)**

***KW END***

**109.** ምህረት: እኔ… ምን እንደምል እንጃ። ማለት የምችለው ነበር ቢኖር እርሶ ህይወቴን እንዳተረፉት ነው።

**110. SAD MOTHER: (sniffles)** ምን ማለትሽ ነው?

**111.** ምህረት: ከሀኪሙ ጋ ሲጨቃጨቁ ሰምቼዎት ነበር። ስለምን ያወሩ እንደነበር አልገባኝም። ግን ስለልጅዎ መገደል የሰማሁ ጊዜ …በቃ ፈራሁ። እና ማድረጉን ተውኩት።

**112. SAD MOTHER:** አንቺም እርጉዝ ነሽ? ልጅት አንድ ነገር ልንገርሽ። ከዛ ክሊኒክ ወጥተሽ መሄድሽ እስከዛሬ ከወሰድሽው ርምጃ ትክክለኛው ነበር።

**113.** ምህረት: እኔንጃ ግራ ተጋብቼያለሁ።…

**114. SAD MOTHER:** ነይ እዚች እድንጋይ ላይ እንቀመጥ እና እናውራ።

**115. SFX: FOOTSTEPS TWO PERSONS**

**116. SFX: WOMAN/**ምህረት **SIT (RUSTLING OF CLOTHES)**

**117. SAD MOTHER:** ስሚኝ እማ ፅንሱን ለማስወረድ ወስኚም አትወስኚ- ይህ አያገባኝም። ለየትኛዋም ሴት ቢሆን መቼም ቀላል ውሳኔ ሆኖ አያውቅም። ግን ለማስወጣት ከወሰንሽ በባለሙያ ዶክተር ጋር መሆን አለበት። የሚያሳዝነው ነገር የእኛኑ አገር ጨምሮ በርካታ የአፍሪቃ ሀገራት ፅንስ ማስወጣትን ጨርሶ ይቃወማሉ። ፅንስ ማስወረድ ህገ ወጥ ባልሆኑባቸው አገሮች እንኳን ሁሉም ሴቶች ትክክለኛ ህክምና የሚያገኙበት ቦታ የለም። ይህም ለሴቶቹ ሁኔታውን አዳጋች ስለሚያደርገው እንደነ ዘሪሁን ያሉ ሰዎች ገንዘብ ለማግኛ እድል ይከፍትላቸዋል።

**118.** ምህረት: ሰዎች ልጅ ማስወረድ ሀጢያት ነው ሲሉ ሰምቻለሁ።

**119. SAD MOTHER:** ይገባኛል። ብዙ ሰዎች እንደዛ ያስባሉ። ግን ለምሳሌ ልጅቷ ተደፍራ ከሆነስ? የእናትየዋ ጤንነት ወይንም ህይወት አደጋ ላይ ከሆነስ? እንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ በርካታ የአለማችን ሀገራት ፅንስ ማስወረድን ይፈቅዳሉ።

**120.** ምህረት**:** እንዴት ይህንን ሁሉ አወቁ?

**121. SAD MOTHER:** ምን ዋጋ አለው! ያሳዝናል። ይህንን ሁሉ ያወኩት እንደው ከረፈደ በኋላ ነው። ቆይ ልጄን ምን ገጥሟት እንደነበር ልንገርሽ…

## 122. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>

ምህረትን እና ሀዘንተኛዋ እናትን እንዲያወጉ እንተዋቸውና እኛም የዛሬውን« መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» የተሰኘውን ሁለተኛ ዙር ተከታታይ ድራማ በዚሁ እናጠናቅ። የምህረትን ውሳኔ እንዴት ትመለከቱታላችሁ? የዳንኤልን ልጅ በሆዷ ለማቆየት ወስናለች። ሆኖም ፤ ላቦሪያ በሚባለው ሩቅ አገር ውስጥ ከእዚሁ ተመሳሳይ ልጅ ጋ አንድ ቀን ህይወት ስለመመስረት የምታስብ ልጅ አለች።– ከዳንኤል ጋር ጋ! እስኪ አልማዝ አሁን የቀረፀችውን አዲስ የቪዲዮ ዘገባ በድረ ገፃችን dw.de/lbe ላይ ተመልከቱ። በተጨማሪም ያላችሁን ሀሳብ በፌስቡክ ገፃችን ላይ አካፍሉን። በሚቀጥለው ጊዜ እስከምንነናኝ ደህና ሁኑ።